የምፅዓቱ መፅሐፍ ቅዱስ HOLY BIBLE የምሥራች

ቅጽ 83 ቁጥር 4(970)

“እርሱ በመንፈሰ ቅዱስ በእሳትም ያጠምቃችኋል” (ማቴዎስ 3፥11)

ከላይ የሚላከው ኃይል

በወንጌላዊ ዮሐንስ ግሪንፊል የሞሪቪያን ወንጌላዊ
By Evangelist John Greenfield (Monrovian Evangelist)

ጌታ እግዚአብሔር መንፈሰ ቅዱስ በዚህ ለምንገኘው እንደቀድመው ፍሰሰ እንደ ጴንጤቆስጤ አለት እንዳረሰረሰከው ዛሬም ቅዱስ መንፈስህ ልባችንን ይለኩሰው። የተሰጠን የተሰፋ ቃል ይጠበቅልን። በሴትና ወንዶች ላይ ያልከው ይድረሰልን። ከላይ የምትልከው ልዩ ሀይል ይፍጠንልን። ያ ሚቀጣጠል ልብና የእሳት ልሳን ይምጣልን። በማያቋርጥ ጸሎትና ምሰጋና ፍቅርህ ይብዛልን።

የሰኮትላንድ የሞሮቪያን የወንጌል መነቃቃት አገልጋዮቹ በ1763 ዓ.ም በተወለደው መዝሙር ደራዲሲ ጄምስ ሞንትጎመሪ የዘመረው ለብዙ ዓመታት የዘለቀ የቅድሰና ልምምዶችን በዚያ ሰፋራ አሰከትሎ ነበር። በሀገራችን ኢትዮጵያም በዛሬው ዘመን ኢሉ አባቦራ በተባለው የወንጌል አርበኛው አናሲሞስ ነሲብ/ሂካ/ በተወለደበት በ1970ዎቹ ተነሳው የመንፈሰ ቅዱስ እንቅሰቃሴን ያለፉበት ዛሬም በመላው ዓለም የተበተኑ የዚያ ሰፍራ ወገኖች ይመሰክሩታል ከዚህም የተነሳ በኢሉ አባቦራ በሌሎች ሰፍራዎች የሚታዩ ማፈናቀሎችና ዘር ተኮር ግድያዎች አይታዩም።

እውነተኛ የመንፈሰ ቅዱስ እንቅሰቃሴ በተከሰተበት ሰፍራ ሁሉ የእርኩሰት የጥላቻ የዝሙት የሌብነት የግድያ ወንጀሎች ይወገዳሉ። የዌልሰ ኢንግላድና አካባቢው የዚህ የመንፈሰ ቅዱስ ሥራ ፍሬዎች ምሳሌ ናት። የእኛ ሠፈር፣ ከተማ ምን ያመሰላል?

የሞሮቪያን የታሪክ ዘጋቢዎች እንደሚተርኩት፥ በሞሮቪያን የወንጌል አገልጋዮች የተካሄዱ እንቅሰቃሴዎች ከተሞችን ያንቀጠቀጡ፣ ክፉ ሰራዎችን የለወጡ የእግዚአብሔር ጎብኝቶች ሆነው ውቅያኖሰን ተችግረው በሰሜን አሜሪካ ለተካሄዱት ታላላቅ መነቃቃቶች /Great Awakening/ መነሻ ምክንያቶች ሆነዋል።

የዚህ አይነቱ የመንፈሰ ቅዱስ እንቅሰቃሴ ጅማሬ የታየው በሐዋርያት ሰራ 8 እንደተገለፀው በሰማርያ ሲሆን ትሩፋቱ ለትውልድ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባውም እንደደረሰ ተፅፏል (ሐዋርያት 8፥27)

በነሐሴ ወር በ1763 ዓ.ም በሰኮትላንድ አውሮፓ የተካሄደውን የመንፈሰ ቅዱስ ታምራት ዛሬም ድረሰ ውጤቱ ህያው ሆኖ በመወሳት ላይ ይገኛል። የክርሰቶሰ አማኞች ሁላችንም የንጉሰ ካህናት በመሆናችን ይህን መሰሉን ጉብኝት በቃልና በፀሎት እናቀጣጥለው። (1 ጴጥሮሰ 2፥5)

መልእክት ከአሳታሚው

(ወንድም ሪክ ካርማይክል By Brother Rich Charmichael Publisher)

የመንፈሰ ቅዱስ የክብር አገልግሎት

The Glorious Ministy of the Holy Spirit

“እንግዲህ እንደጥበበኞች እንጂ ጥበብ እንደጎደላቸው ሳይሆን እንዴት እንድትመላለሱ በጥንቃቄ ተጠበቁ። ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ። ሰለዚህ የጌታ ፈቃድ ምን እንደሆነ እሰተውሉ

እንጂ በወይን ጠጅ አትሰክሩ። ይህ ማባከን ነውና መንፈሰ ይሙላባችሁ።" (ኤፌሶን 5:15-18)

የአማኞች ዋነኛው የህይወታችን ክፍል በዚህ በመጨረሻው ዘመን በቅዱሰ መንፈሰ መሞላታችን ነው።

ለእራሳችን በመንፈሰ ቅዱሰ መሞላት ብቻ ሳይሆን ለሌሎች በዚህ ክፉ ዘመን በጭንቀትና በመከራ ላሉትም እንድንዳርሰ በጌታ ተልከናል።

ሠይጣን ጊዜው እንዳጠረበት በማወቅ በተቻለ መጠን ይህን የከበረ አገልግሎት ባግባቡ እንዳንፈፅም ልዩ ልዩ መሰናክሎችን፣ እንቅፋቶች፣ ሰህተቶችን እየላከብን ይገኛል።

ብዙዎች ያመኑ የነበሩ ሰዎች በዘመኑ እርም እየተያዙ ከክብር ሲወርዱ በዓለም ምናምንቴ ተይዘው በአሳዛኝ ፍፃሜ ሲያልፉ በማየት ላይ እንገኛለን።

ይህን በማገናዘብ ይህ የመንፈሰ ቅዱሰ የክብር አገልግሎት እንዳይጎድልብን እንዳይጠፋብን በቃልና በፀሎት በውነተኛ ንሰኃ ልባችንን እንጠብቅ፤ ሌሎቹንም እንርዳ።

ጌታችን ኢየሱሰ ክርሰቶሰ ተከታዮቹ ቃል የተገባላቸውን መንፈሰ ቅዱሰ እንዲቀበሉ የተናገረው ለዚህ ለእኛም ዘመን እማኞች የሚሰራ የተሰፋ ቃል ነው። የመንፈሰ ቅዱሰ የተሰፋ ቃልና ሰራዎች በጌታችን በኢየሱሰ ክርሰቶሰ አገልግሎት ከእናቱ ማህፀን ጀምሮ እየፈሰሰ ለብዙዎች ማነቃቃትና መሰማራት መነሸ ሆኖ የታየ የተመሰከረለት ነው (ሉቃሰ 2፥27፥18)

ጌታችን ኢየሱሰ ክርሰቶሰ ለአገልግሎት በተሰማራበት ወቅት ሁሉ ሰራዎቹ የመንፈሰ ቅዱሰ የክብር አገልግሎትን የተከተሉ ሰዎችን ከአጋንንትና ከደዌ የሚፈወሱ ኃያል እንቅሰቃሴዎች ነበሩ (ማቴዎሰ 12፥28፣ ሐዋርያት 10፥38)። ጌታ መንፈሰ ቅዱሰ ለአገልግሎት ኃይልን ምሪትን ሰጦታዎችን እንደሚሰጠን ሁሉ በደከምንበት ወቅትም የሚያነቃቃን አጋር አለኝታችን ነው (ሮሜ 8:26)

ሰለዚህም ለተሳካ የክርሰትና ህይወት ለተጠራንበት የቅዱሰ ወንጌል ህይወት በመንፈሰ ቅዱሰ በእየእለቱ እንሞላ እንመላ ለሰ (ሮሜ 8፥14፣ ገላትያ 5፥25)

ሙሉ ደኅንነት በክርሰቶሰ ከፍተኛው ጥቅማችን ነው

(በእንድሪው ሙሬ)

ወንጌላችንም ሆነ የክርሰቶሰ ፀጋ ሙሉ የሆነ የማይቀናነሰ የእግዚአብሔር ሰጦታ ነው።

የፕሬሰቢተሪያን ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የነበር ዲሞሰ ሻካርያን የነበረበት ቤተክርሰቲያን መንፈሳዊ ልምምድ ያድግ ዘንድ በየፓርኩና አዳራሾች የወንጌል ሰብሰባዎችን በአሜሪካን ሀገር ጀመረ።

በዚህ ድንቅ አገልግሎቱ አያሌ የቢዝነሰ ሰዎች ምሁራን ጭምር እየጎረፉ ባሉበት አንድ የጸሎት ምሽት ላይ ዶክተር ራይሰ የተባለ የጌታ አገልጋይ "Full Gospel is the means" "ሙሉ ወንጌል መፍትሄ ነው" የሚል ቃል መጥቶለት "Full Gospel Business men" የተባለ ወንጌል ደጋፊ ማህበር መሥርቶ የወንጌሉን ሰራዎች ብዙ ደገፈ። ቆይቶ ይህ ሰያሜ አጥቢያ ቤተክርሰቲያን/ዲኖሚኔሽን መጠሪያ ለመሆን በቃ።

የወንጌሉ የፍቅር የምህርት ቃል ሳይጎድል በሙላት መሰበክ ይኖርበታል። ሰነፍ ደካማ የሆነው የሰዎች ልብ ፀጋን ብቻ መሰማት ለሚፈልገው ጸጋውን እምቢ ለሚሉ ፍርድ እንዳለም መሰበክ የተገባ ነው። የወንጌል ተሀድሶ ጀማሪ ማርቲን ሉተር እንዳሰተማረው ትክክለኛ ሚዛናዊ ሰብክት ህግና ወንጌል ያሟላ ነውና ሰባኪዎች ህጉንም የወንጌል ምህርቱንም አጣምረን እንሰበክ።

ብዙዎች መዳን ያገኙበት በራሪ የወንጌል ፅሑፍ "ህይወት ወይም ሞት" ትክክለኛ ምሪት አላት።

በሉቃሰ ወንጌል ጌታ ያቀረበልን ሁለቱ ልጆች የህግና የወንጌሉ ምሳሌዎች ናቸው። በህጉ የበደለ ይቀጣል ንሰሃ የገባ ምህረት ያገኛል። ይህን ተረድቶ በጌታ ምህረት ወደ ፍቅሩ ቤት መመለሰ ትልቅ ማስተዋል ነው።

የእግዚአብሔር ልጅነትን በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ማግኘት ከሰጦታዎችና ከበረከቶች ሁሉ የላቀው ነው።

ምድራዊ አባት ልጆቹን ከሚወደው በላይ እግዚአብሔር እኛን አማኝ ልጆቹን ያፈቅረናል። (1ኛ ዮሐንስ 4፥8)

ጌታ እግዚአብሔር ባገኘን መከራ ሁሉ መሸሸጊያ መጠጊያ አምባችን ነው። ይህ አምባ ጌታ ክርስቶስ ባለንበት ሁኔታ የሚደርሰልን መሆኑን በህይወታችን የቀመሰን የተረዳን ይህንን ለሌሎች የመመስከር የመንገር ልዩ ኃላፊነት፣መብት፣ግዴታና ጥቅም አለን።

“ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ፀጋ ተገልጦአልና ይህን በሙሉ ተናገረና መስክር ገስጽም።” (ቲቶ 2፡12)

የመቀደሰ ቃል ኪዳን

“ትቀደሱም ዘንድ ፈልጉ ያለእርሱ ጌታን ሊያይ የሚችል የለምና” (ዕብራይሰጥ 12፥14)

የመናኛ ጉዞ ጸሀፊ ዮሐንስ ቡንያን እንደ እርሱ ቅድሰናን የፈለገ ክርስማስ ኢቫን የተባለ አገልጋይ የገለጸው የቅድሰና ትልቅ ምክር የክርሰትና በረከት ምንጭ ቅድሰና መሆኑን ነው።

እማኞች በሕይወት ጉዟቸው ድርቀት ውድቀት ድካም ሲሰማቸው በቅድሰና ልምምድ መካፈልና ከክፉ ሀሳብና አካባቢ በመራቅ የጌታን ክብርና ኃይል ይጎናፀፋሉ። በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም በሚደረግ ጸሎትና እንቅሰቃሴ የእግዚአብሔርን ክብር ለማየትና ለመቀበል ብቸኛው መንገድ ቅድሰና ከክፉ ሀሳብ፣ ሰው፣ ሰፍራ፣ እቅሰቃሴ መለየት ነው።

ጌታችን በተደጋጋሚ በመጽሐፍ ቅዱሰ የጠቀሳቸው አገልጋዮች ብርቱ የሆነው ዓለምን ሰይጣን ሰጋን ማሸነፍ የቻሉት በራሳቸው ጥበብ፣ እቅምና ማሰተዋል ሳይሆን በቅድሰና ከዚህ ዓለም ክፉ ልምምዶች በመለየት ነው።

ከሚዋሹ ጋር አብረን እየዋሸን ከሚሰርቁ ጋር አብረን እየሰረቅን፣ ከሚያመነዝሩ ጋር አብረን እያመነዘርን፣ በሀሳብም በድርጊትም የዓለምን ወዳድ እየሆን እግዚአብሔርን አገለግላለሁ የሚል ውሸታም ክርሰቲያን ነው። መቼም እግዚአብሔርን አያይም። የእግዚአብሔር እውነተኛ ክንድና በረከቱ በዚህ ዓይነት ሰው ላይ አይገለጥም። የገንዘብ ብዛት የሰኬት መጨመር በሰዎች ታዋቂ ተወዳጅ መሆን የእግዚአብሔር መለያ ምልክቶች አይደሉም።

የእግዚአብሔር መሆን የሚገለጸው፣ የሚለካው በቅድሰና ከዓለም ሰንለይ፣ የሰጋ ሥራዎችን ሰንጸየፍና ሰንርቅ፣ የሰይጣንን እጀንዳዎች በጸሎትና በቃል ሰንቃወም ብቻ ነው።

በዓለም ሚዛን በሚዲያ ታዋቂ እየሆኑ የመጡ ሰዎች ከዓለም ሥራዎች ካልተለዩ የሥጋን ሥራዎች ካላወገዙና ካልራቁ በምንም መልኩ ቅድሰና የሌለባቸው የዓለም ወዳጆች ናቸው። “ዓለምን መውደድ ለእግዚአብሔር ጥል እንደሆነ አታቁምን” (ያዕቆብ 2፥4)

“የእግዚአብሔር ሰው ሆይ ከዚህ ሻሽ ጽድቅንና እግዚአብሔርን መምሰል እምነትንም ፍቅር መጽናትንም የዋህነትንም ተከታተል። (1ኛ ጢሞቲዎስ 6፥11)

ሕይወታችሁን በእግዚአብሔር ቃልና መንፈሰ መዝኑ

(በመንፈሳዊ መነቃቃት አገልጋይ ዌስሌ)

እግዚአብሔር እንደሚመዝነው ሕይወታችንን መመዘን አሰቸጋሪ ይሆንብናል። እኛ ሕይወትን ምንመዝነው በጊዜያዊ ምድራዊ ሰጋዊ ውሱንና ጠፊ መሰፈርቶች ሲሆን እግዚአብሔር ሕይወታችንን የሚመዝነው መንፈሳዊ በዘላለማዊ በማይጠፋ ወሰን በሌላው ሰማያዊ መሥፈርቶች ነው።

በእግዚአብሔር መለኪያ ሕይወታችንን መመዘን የምንጀምረው በዓለማዊ ሥጋዊና የሰይጣን ቅንብሮች በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ድል አግኝተን የእግዚአብሔር መንፈሰ ሁልጊዜ ሲያንቀሳቅሰን

ሲሞላብን ነው። (ሐዋርያት ሥራ 2፥38 /ኤፌሶን 5፥18)

መንፈሳዊ ሕይወት የሚገኘው ቅዱስ መንፈስ በሚሰጠው ልዩ ሥራ ነው። መንፈሳዊ ለመሆንም ከእግዚአብሔር ዳግም መወለድ ግድ ይላል። (ዮሐንስ 3፥8)

ከዚህ ከእግዚአብሔር በመንፈስ ከመወለድ ውጭ አንዳች መንፈሳዊ ሕይወት በሰዎች ዘንድ-አይከሰትም። “የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ከሆነ ግን ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም”(ሮሜ 8፥9)

በክርስቶስ የሆነ ሁሉ የክርስቶስ መንፈስ ሲኖረው በአንዳንዶች ደግሞ ከራሳቸው አልፎ ለሌሎች የሚተርፍ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የሚገለጸው በመታዘዝ በቅድስና በመጠበቅ በጸሎት በመትጋት ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣልን መንፈስ ቅዱስ እንዲሞላን እንዲበዛልንም ነው። (ዮሐንስ 10፥10)

መንፈስ ቅዱስ ራሱ አምላክ የሆነ ከብሉይ ጀምሮ ሰዎችን ለእግዚአብሔር ሥራ የሚቀድስ ጌታ ነው።(1 ተሰሎንቄ 5፥23)

በእግዚአብሔር ቃል የክርስቲያኖች ሕይወት እንዲመዘን ከጥንት ጀምሮ የእግዚአብሔር ሰዎች ሲናገሩ ሲሰብኩና ሲጽፉ ኖረዋል።

የአውሮፓና የአሜሪካ መንፈሳዊ መነቃቃቶች በጉልህ የሚጠቀሰው ጆን ዌስሌ በዘመን ተሻጋሪ መዝሙሮቹ ይህንን የመንፈስ ቅዱስ የኃይልና የማቀጣጠል ሥራ ገልጾታል።

> ቅዱስ የእግዚአብሔር እሳት በእኔ ላይ ተገለጽ እንዳልሳሳ የውሰጥ መሻቴ ሁሉ ለጌታ ይገዛ ነፍሰና መንፈሴ ሁሉ እንዳይንዛዛ እሳቱ ይቀጣጠል በመንፈስ ቅዱስ ሁለመናዬ በክርስቶስ ደም ይቀደስ

ሕወታችንን በሚያነጻው በሚያነቃቃው በጌታ መንፈስ በቃሉ መመዘን ዛሬም ይቻላል። “ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንት ዛሬ እስከለዘላለም ያው ነው።” (ወደ እብራውያን 13፥8)

በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላትና ሕይወታችንን ለመመዘን ምንም ተጨማሪ ፎርሙላ የማያሰፈልገው የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎችን ከሐዋርያት ሥራ በማንበብ ባለንበት መንደር ከተማና ሀገር ልምምዱን መጀመር እንችላለን። ዋናው ነገር መንፈሱን መጠማት ነው። (ማቴዎስ 5፥6/ ኢሳይያስ 55፥1)

ለመንፈሳዊ መነቃቀት ጸሎት እና የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ሂደት

የመንፈስ ቅዱስ ሙላትና የእግዚአብሔር ሕዝብና ጉባኤ በመንፈሱ መነቃቃት ከብሉይ ኪዳን ዘመን ጀመሮ እስከ ዛሬ ሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን መገባደጃ ድረስ በመከናወን ላይ ነው።

የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ሰፍራ ጂኦግራፊ ባህል ሳይገድቡት ጌታ በወደደው መንገድ ልባቸው ለጌታ በተሰጡ ቅዱሳን ሁሉ በዓለም ዙሪያ ይካሄዳል።

የመጀመሪያው በመጽሐፍ ቅዱስ የተዘገበው የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ እግዚአብሔር የጠራው ሕዝቡን ከክፉ ጠላት የጠበቀበት በሕዝቡ በር ላይ የተረጨው የበጉ ደም ውጤት ነው። (ዘጸአት 12፥24) ሁለተኛው የመንፈስ ቅዱስ የብሉይ ኪዳን እንቅስቃሴ በንጉስ ዳዊት መንገድ እንደሄደ የተጻፈለት ንጉስ ኢዮስያስ የእግዚአብሔርን ቃል መጽሐፍ ከካህኑ ኬልቅያስ በመቀበል ሕዝቡን በመንፈስ ቅዱስ በማነቃቃት እርኩሰትን በመካከላቸው በማሰወገድ እግዚአብሔርን ያከበሩበት የመታደስ ወቅት ነው (2 መዋእል 34)

በነብያቱ ዘመን ከምርኮ እንዲመለሱ በጌታ ቃል መቅደሱን እንዲሰሩ ያደርጉዋቸው እንቅስቃሴዎች ሁሉ የመንፈሳዊ መነቃቃት ሥራዎች ነበሩ።

በአዲስ ኪዳን የመንፈሳዊ መነቃቃት የተጀመረው ጌታ ከተሰቀለ ከሞተና ከተቀበረ በኋላ ደቀመዛሙርቱ ተሰፋ ቆርጠው ሳሉ በጭንቀት በተዘጋ ቤት በብዙ ጸሎት የጌታን ፊት ሲፈልጉ መንፈስ ቅዱስ ከላይ በመውረድ ነፋሳትን በሺዎች ወደ ጌታ መንግስት ባሰገባበት ፈርተው ተደብቀው የነበሩ ደቀመዛሙርት በኃይልና በሰልጣን መመሰከር በጀመሩበት ወቅት ነው። (ሐዋርያት ሥራ 2)

ከሐዋሪያት ሥራ በኋላ እንደተጻፈው በእግዚአብሔር መንጋዎች ውስጥ የገቡ ተኩላ ሐሰተኞች ብዙ ክፋት እያደረሰ ቤተክርስቲያን ከክፉ መንግስታት ጋር በመጣመር ከፍተኛ ሰደት መከራ የደረሰበት ወቅት ነበር። በእነዚያ ወቅቶች የካታምቦ ሰማእታትና የመሳሰሰሉት በክርሰቶስ በማመናቸው እየተሰየፉ ወንጌሉ ለትውልድ ቀጥሎ የመካከለኛው ዘመን ተሃድሶ ድረሰ ቀጥሏል።

በመካከለኛው የተሃድሶ ዘመን ማርቲን ሉተር ጀንካልቪንና የመሳሰሉት ቤተክርስቲያን ወደ ቃሉ እንድትመለሰ ብዙ መከራን በመቀበል ተጋድለው ዛሬ ወንጌላዊያን አማኞች በሚከተሉት በክርሰቶስ እምነት በእግዚአብሔር ጸጋ በመንፈሰ ቅዱሰ ሥራ የተሞላንበት ዘመን መጣልን።

የመዳንም የመንፈሰ ቅዱሰ ሙላትም ሂደት

ለመንፈሰ ቅዱሰ ሙላትና ለመዳን ምንም ልዩ ቅንብር የማይጠይቅ ቅዱሰ ቃሉን የተከተለ የቃሉ ሕይወትና የልብ ንሰኃ ነው።

1. መናዘዝ - ሐዋርያት ሥራ 2፥38
2. መጠይቅ (ጌታን) - ሉቃስ 11፥13
3. ጌታን መቀበል - ዮሐንስ 1፥12/ ማቴዎስ 11፥24
4. መታዘዝ - ሐዋርያት ሥራ 5፥32

ከመንፈሰ ቅዱሰ ጋር ኅብረት - በቶዘር

Fellowship with the Holy Spirit, A Tozer

በማንኛውም አካል ወይም ልዕልና ሁኔታዎች የሚወሰን አብሮ የሚቆመው የሚኖረው ወይም የሚቆራኛው ነው።

በሀገራችን ምሳሌዎችም እንደሚታወቅ ከመልካም ሰው ከዋሉ መልካምነት ከክፉ ሰው ጋር ከዋሉም ክፋት ከሰው ላይ እንደሚሰለጥን በተጨባጭ ይታወቃል።

አማኞችም የዘመድ የጓደኛ የሥራ ባልደረቦች ቢያሰፈልጓቸውም ለራሳቸው ሕይወትም ሆነ ለሌሎች ሕይወት መንፈሳዊ ሰኬት ትልቁ ወዳጅነትና ህብረታቸው ከመንፈሰ ቅዱሰ ጋር መሆኑ እጅግ የሚታመንበት ነው።

ቅዱሰ ቃሉ ፍጹም ህብረትና አንድነት በአብ በወልድና በመንፈሰ ቅዱሰ ዘንድ እንዳለ የእኛም ህብረት ከአባት እግዚአብሔር ከልጁም ከጌታ ኢየሱሰ ጋር የሚሆነው በመንፈሰ ቅዱሰ ህብረት ብቻ ነው። “እናንተ ደግሞ ከእኛ ጋር ሕብረት እንዲኖራችሁ ያየነውን የሰማነውን ለእናንተ ዳግም እናወራላችኋለን። ኅብረታችንም ከአባት ጋር ከልጁም ከኢየሱሰ ክርሰቶስ ጋር ነው።” (1ኛ ዮሐንስ 1፥3)

በዚህ ዘመን የገጠመን ችግር ጌታን እምነን መከተል ከጀመርን በኋላ በዝምድና በሥራ ቦታ ወይም በጥቅምና ሁኔታዎች ህብረታችን ከክርሰቶስ ተከታዮች ይልቅ በዓለማውያን ጋር መብለጡ ነው። ሰይጣን የእርሰበርሳችንን ድካም እየጎላ እንዳንቀባበል እንድንገፋፋ ሰለሚያደርገን በዚህ ነቅተን ህብረታችንን መጀመሪያ ከመንፈሰ ቅዱሰ ጋር በማድረግ ከወገኖች ጋር ህብረት ይኑረን፣ እንተማመን።

ሌሎች ወገኖቻችን እንደሰው መሆናቸውን ሰሜት እንዳላቸው ሊሳሳቱ እንደሚችሉ እንረዳ።

በተደጋጋሚ ወገኖች የሚያሳዝኑን ከሆነም እንደቃሉ መጀመሪያ ራሳችን ፊት ለፊት ነግረን ካልተሰተካከሉ ለቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ታላቆች በፍቅር እንዲታረሙ እናሰመክር። (ማቴዎስ 18፥21)

እኛ እራሳችን ከመንፈሰ ቅዱ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ካለን በየምክንያቱ በወገኖቻችን ደረሰብን የምንለውን መጎዳት የማለፋ፣ የማነጽ፣ በማሰወገድና የመቻል ብቃቱን መንፈሰ ቅዱሰ ያጎናጽፈናል። የእምነታችን ጀማሪና ጌታችን ኢየሱሰ ክርሰቶስ ከአባቱ አብና ከመንፈሰ ቅዱሰ ጋር የነበረው ያለው የሚኖረው ሕብረቱ ለእኛ ትልቅ ሕያው ምስክር ነውና እንሞላው።

በሐዋርያቱ ዘመን ያመኑትን ጌታ በቅዱስ መንፈሱ በቃሉ የተናገራቸው የመንፈስ ቅዱስና የጌታ ሕብረት መሀሪ ይቅር ባይ ፈዋሽ መሆኑን ይመሰክራል። “የመንፈስ ቅዱስን የተሰፋ ቃል ከአብ ተቀብሎ ይህን እናንተ አሁን የምታዩትንና የምትሰሙትን አፈሰሰው።” (የሐዋርያት ሥራ 2፥33)

በእኛና በጌታ መንፈስ ቅዱስና በወገኖች መካከል ሕብረት እንዲቀጥል በአንድ ሀሣብ እንደቃሉ እንሰማማ። (የሐዋርያት ሥራ 1፥14)

በመንፈስ ቅዱስ ስለመጸለይ - በቶሬ

Praying in the Holy Spirit – R.A – Torra

“በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ፤ በዚህም አሳብ ሰለቅዱሳን ሁሉ እየለመናችሁ በመጽናናት ትጉ።” (ኤፌሶን 6፥18)

ከዚህ የእግዚአብሔር ቃል ውስጥ እጅግ ልናተኩርበት የሚገባው በመንፈስ የሚለው ነው። ይህን አባባል በብዙዎቹ ወሳኝ የእግዚአብሔር መልክቶች ውስጥ እናነባለን በመንፈስ ልንጸልይ የምንችለው ጌታችን እንዳዘዘን ስልጣን ባለው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በመጸለይ የከበበንን ኃጢያትን ክፉ መንፈሳዊ ሰልጣናትን በመሰበር ነው።

“በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ” (ዮሐንስ 14፥14)

እግዚአብሔርን በልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጠየቅ ማመሰገንና መማጸን በመንፈስ ቅዱስ መጸለይ ነው። ይህ ደግሞ ጌታችን ከሰጠን ታላላቅ ተሰፋዎች መካከል አንዱ ነው።

በመንፈስ የመጸለይ ዋነኛና ልዩ ምልክቱ የእግዚአብሔርን ክብርና ሥራ በሕይወታችን የማየት የሌሎች ሰዎች መዳንን ከልብ የመፈለጋችን ጉዳይ ነው።

“መንፈስ ድካማችንን ያግዛል እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል” (ሮሜ 8፥26)

በምናየው በምንሰማው ነገር ልባችን ሲታወክ የጌታን እርዳታ ስንፈልግ መንፈስ ቅዱስ የጸሎታችንን ትክክለኛ አቅጣጫና ውጤት ያሳየናል ያመለክተናል።

በጸሎታችን እግዚአብሔር እሰመሰሰልን ድረስ የቱንም ያህል ጊዜ ቢወስድ በጽናት መቀጠል ለጸሎታችን መልስ ያስገኛል። “በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ቅዱስ ጸልዩ። በዚህም አሳብ ሰለ ቅዱሳን ሁሉ እየለመናችሁ በመጽናት ሁሉ ትጉ” (ኤፌሶን 6፥18)

በጸሎት በጌታችን ፊት በምንወድቅበት ሰዓት የራሳችንን ፈቃድ ሁሉ በመተው ጌታ በፈቃዱ ርእሰ አቅጣጫና የጸሎት ርእሰ እንድንሰማራ ቅዱስ ቃሉንና በመንፈስ ቅዱስን ድምጽ ከወገኖች ከጸሎት አጋሮቻችን እንቀበል “እኛም ለዚህ ነገር ምስክሮች ደግሞም እግዚአብሔር ለሚታዘዙ የሰጠው መንፈስ ቅዱስ ምስክር ነው። (ሐዋርያት ሥራ 5፥32)

በጸሎት በምንሰማራበት ወቅት መታመኛችን የጸሎት ሕብረቱ የመሪ የምንላቸው አገልጋዮች ወይም የራሳችን ማሰተዋልና መሻት ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ላይ ብቻ እንታመን።

እያሌ የጸሎት ሥራዎች ቀንበሮች ሰብረው ስንሰለት በጣጥሰው እርምና ነውሮች የሚወገዱት መመኪያችን ኃይላችንና ብርታት ሳይሆን የጌታ መንፈስ ብቻ ሲሆን ነው። “በመንፈሴ እንጂ በኃይልና በብርታት አይደለም” (ዘካርያስ 4፥6)

ዓለም አቀፍ የጸሎት ርእሶችና ምስክርነቶች

ከጃፓን

መንፈሳዊ ሕይወቴን ስለሚያነቃቃው የምጽአቱ የምስራች ጋዜጣችሁ ጌታን እጅግ እመሰግናለሁ። በመጋቢትና ሚያዚያ 2016 የቀረበው እራሰን የመካድ መልእክታችሁ ሕይወቴን ለውጧል ተባረኩ። ጋዜጣችሁን መላኩን አታቋርጡብኝ።

ከካናዳ

በየሁለት ወሩ የምትልኩልኝ ጋዜጣችሁ ለመንፈሳዊ ሕይወቴ ብዙ ጥቅም አስገኝቶልኛል። በዚህ ወር ጌታ ከሰጠኝ ለአገልግሎታችሁ ድጋፍ የላክሁትን ሰጦታ በፍቅር አቀርባለሁ።

ከእንግሊዝ

ስለምትልኩልኝ አበረታች አነቃቂ መንፈሳዊ ጋዜጣ እጅግ ላመሰግን እወዳለሁ። መንፈሰ ቅዱሰ ዘወትር የምትልኩልኝ ጋዜጣ መልክቶች ሕይወቴን እያነቃቃው ይገኛል።

ከፊሊፒንሰ

ከ1988 ዓ.ም ጀምሮ የምጽአቱ የምሥራች መንፈሳዊ ጋዜጣ ታዳሚ ነኝ። ይህን ህይወትን የሚያንጽ ጋዜጣ እንድታዘጋጁ የረዳችሁ ጌታ ይባረክ።

ከናይጄሪያ

የምጽአቱ የምሥራች ለእኔና ለቤተሰቤ እሰደናቂ መንፈሳዊ ማዕድ ነው። አገልግሎታችሁ የበለጠ እንዲባረክ ጌታ በሁሉም አቅጣጫ እንዲባርካችሁ እዚህ ካሉ ወገኖች ጋር እጸልያለሁ።

ከካንሳስ

የመጋቢትና ሚያዚያ 2016 እትም ለእኔ በግል የተጻፈልኝ እስኪመሰለኝ ድረስ እያነበብኳቸው በጣም ተባርኬአለሁ። አሁን ያለሁበትን ሁኔታ እያመለከተ በድል ፈተናዎችን እንድወጣ ያደረገ የጌታ መንፈሰ ቅዱሳን ኃይል አግኝቼበታለሁ። ጋዜጣችሁን ሳታቋርጡ ላኩልኝ።

ከመቱ ኢሉ አባቦራ

የምጽአቱ የምሰራችን ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጀምሮ የምከታተለው አሰተማሪ መንፈሳዊ ጋዜጣ ነው። በዚህ ካሉ ወገኖች ጋር በጸሎት ሕብረት እንጠቀምበታለን። የእንግሊዘኛውንም የአማርኛውን እትም በመላክ ትብብራችሁ ይቀጥል።

ለመላው እንባቢዎቻችን

ለየምጽአቱ የምሥራች ስለምታቀርቡት ምስጋና ጌታን እናመሰግናለን ተባረኩ። ለሁላችሁም በግል ለመመለስ እቅም ስለሌለን በዚሁ ምስጋናችን ይድረሳችሁ።

የአገልግሎቱ ብቻኛው ገቢ የእንባቢዎች መዋጮ በመሆኑ የምትችሉትን በፖስታ ቤት፣ በሀዋላ በመላክ ለሌሎች ጠያቂዎቻችን ለመላክ እንድንችል ትብብራችሁን በጌታ ፍቅር እንጠይቃን።

የምጽአቱ የምሰራች የወንጌል አገልግሎት

የፖ.ሣ.ቁ 8986 አዲስ አበባ

የሰልክ ቁጥር 0911 25 19 12

ኢትዮጵያን በእግዚአብሔር የታሰበች ናት

የተርጓሚውና አሰተባባሪው መልክት (ኤዲ/አደፍርስ/ ሀብቴ

“ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች” (መዝሙር ዳዊት 67፥31)

ኢትዮጵያ በታሪካዊ ቅዱሳት መጽሐፍት ተደጋግማ የተጠቀሰች በአንድ ወቅት ዛሬ የአትላንቲክ ውቅያኖስ የአትላንቲክ ውቅያኖስ የተባለው የምትጠራበት በመጽሐፍ ቅዱስ መጀመሪያ ክፍል ላይ የሰው ዘር እንደተፈጠረባት ያረጋገጠባት በአርኬዎሎጂ በጥንት ታሪኮች ቀዳሚ ሀገራችን ናት (ዘፍጥረት 2፥13)

በጥንታዊ ቋንቋዎች “ኩሽ” በእብራይስጥ “ሀበሻ” በአረብኛ “ኢትዮጵ” በግሪክ የተሰጣት ሀገራችን እጅግ አስገራሚ አሰደናቂ ታሪክ ያላት ሀገር ነች።

ትልቁ ጉዳይ ኢትዮጵያ በእግዚአብሔር ቃል መታወቋ ለዓለም ሁሉ የመጣውና በመሰቀል መከራና ሞቱ የሰው ልጆችን ያዳነው ጌታ ክርስቶስን ቀድመው ካወቁ የዓለም ሕዝቦች በእንዱ ዜጋዋ የተነሳ መቀበልዋና በክርስቲያን ሀገርነት መታወቅዋ ለሌሎችም ቀድሞ ለነበረው የይሁዲ ኃይማኖት ተከታዮቹ ሲሰደዱ በደግ ንጉሰዋ የተቀበለቻቸው፣ የእስልምና ኃይማኖትንም የተቀበለች ሀገር ናት። (የሐዋርያት ሥራ 8፥27)

ይህ ሁሉ ከተዘረዘረ በኋላ ግን በዛሬው ወቅት ሰለኢትዮጵያ የምንሰማው የምናየው እጅግ የሚያሳዝን የሚያሳፍር የሚያሰለቅሰም ቢሆን ዛሬም ኢትዮጵያ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ተሰፋ አላት። (እብራውያን 13፥8)

ወደ ሩቅ ምስራቅ እስያ ሲጓዙ በአውሎ ነፋስ ግፊት መርከባቸው የተሰናከለ ሁለት አማኝ የሶርያ ወጣቶች ፍሬምናጦስና አደሰዮስ በንጉስ የባህር ጠባቂዎች ተማርከው ባርነት ሲጠብቃቸው ንጉሱ ኢሳና በመልካምነት ተቀብሏቸው ክርስትናን ለመጀመሪያ ጊዜ ከተቀበሉት ሀገሮች እንዱ ኢትዮጵያ ሆናለች።

ምንም እንኳን ክርስትና በነገስታቱ ከሮማ ቄሳር ጀምሮ ከፖለቲካ የተጣመረ ዛሬም ድረስ የክፋት መሳሪያ ቢደረግም እውነተኛው የክርስትና ወንጌል ግን ለነገስታቱም ለባሮች የፍቅር የነጻነት የእኩልነት መልዕክት መሆኑን በእውነትና በመንፈስ የሚያመልኩና የሚኖሩ ሁሉ ያውቁታል።

እንደነፍሬምናጦስ እቅጣጫውን ወደጓደኛው እናሲሞስ/ሂካ ትውልዱ ኢሉ አባቦራ ሲያቀና በክረምት ምክንያት በአዲሰ አበባ የዘገየው ቻፕሊያን ፓስተር ካርል ሰደርስኪት የመጀመሪያዋ ወንጌላዊት ማህበር ቆይቶ መካነ ኢየሱስ የተባለችው በኢትዮጵያ እንድትመሰረት እብቅቷል።

ስለዚህ የቀደመውን ያልተለወጠውን የክርስቶስ ወንጌልን በዚህ ትርጉም ሥራ ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ የቀጠለውን በፀሎትና በሚቻለን ሁሉ እንደግፍ።

እደፍርስ ሀብቴ መካሸ ተርጓሚና እስተባባሪ
አልማዝ አሳየና ኩመራ ወልዴ
የኢትዮጵያ ተጠሪዎች
እርት አትና ቅንብር
የፖ.ሣ.ቁ 8986 አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ